the women's
the royal women's hospital

# የአፍሪካ ሴቶች ክሊኒክ

## ወደ ክሊኒክ መምጣት የሚችለው ማን ነው?

ማንኛውም የሴት ብልት ግርዛት (ባህላዊ መቁረጥ) ያጋጠማት (የተገረዘች ሴት) በእድሜ ምንም ይሁን ምን ወደ ክሊኒኩ መምጣት ትችላለች። ወጣት፣ እርጉዝ ወይም በእድሜ የገፋና ስለ ግርዛትዎ ማውራት ከፈለጉ መምጣት ይችላሉ።

ብልትዎ እንዲከፈትልዎት የቀዶ ህክምና ሂደት እንዲደረግልዎት ከፈለጉ (deinfibulation ይባላል) እዚህ ሊደረግልዎት ይችላል።

እርጉዝ ከሆኑ ከ34 ሳምንታት ጽንስ በፊት መደረግ አለበት።

በዚህ ክሊኒክ ሌላ ምንም ዓይነት ቀዶ ህክምና አናካሂድም።

ክሊኒኩ የሚከፈተው ዓርብ ነው።

## እርስዎን እንዴት እንከባከባለን

የአፍሪካ ሴቶች ክሊኒክ የሴቶች ግርዛት ወይም ባህላዊ ቆረጣ ያጋጠማቸው ሴቶች የመንከባከብ ልምድ ባላቸው ነርሶች/አዋላጆች የሚካሄድ ነው።

ስለ ጤናዎ እና ስለግርዛትዎ ከርስዎ ጋር ይነጋገራሉ። እነሱ የቀዶ ጥቀና ሂደቱ ፣ ከቀዶ ህክምናው በኋላ ስለሚሰማዎት ለውጥና ስለማገገሚያዎ ይገልጹልዎታል።

እነሱ በተጨማሪ በማንኛውም ሌላ የጤና ጉዳይ ላይ መረጃ እና ድጋፍ ይሰጡዎታል።

የቤተሰብ እና የወሊድ መብት ትምህርት ፕሮግራም (FARREP) ሰራተኛ በቀጠሮዎ ላይ ሊረዳዎት ይችላል።

**የሜዲኬር ካርድ** ካለዎት፣ አገልግሎቱ በነጻ ነው።

የሜዲኬር ካርድ ከሌለዎት፣ እባክዎ ከ FARREP ሰራተኛ ጋር ይነጋገሩ። በዚህ ስልክ ቁጥር (03) 8345 3058 ልትደውሉላቸው ትችላላችሁ።

## ቀጠሮ መያዝ

ወደ ክሊኒኩ ለመምጣት በአካባቢዎ ሀኪም (GP) መላክ አያስፈልግዎትም።

ቀጠሮ ለመያዝ FARREP'ን በስልክ (03) 8345 3058 ያነጋግሩ።

የእርስዎ የቤተሰብዎ ሐኪም ወይም የማህበረሰብ ጤና ነርስ ወደ (03) 8345 3036 (መላኪያ ሪፈራል) ፋክስ በማድረግ ሊያስተላልፍዎት ይችላሉ።




**እባክዎን በቀጠሮዎ ላይ አስተርጓሚ የሚያስፈልግዎት ከሆነ ይንገሩን።**

ከ1 በላይ ቀጠሮ ሊኖርዎት የሚችለው፡

- በመጀመሪያ ቀጠሮ፡ ስለ ጤና ታሪክዎ እናነጋግርዎታለን።
- በሁለተኛ ቀጠሮ፤ የቀዶ ጥገና ሂደቱን እናደርጋለን።
- በሶስተኛ ቀጠሮ፡- ከቀዶ ጥገናዎ በኋላ የማገገምዎን ሁኔታ እንከታተላለን።

አንዳንድ ጊዜ፣ ቀዶ ጥገናውን በመጀመሪያ ቀጠሮ ላይ ማድረግ ይቻላል።

## በቀጠሮዎ ላይ ምን ይፈጠራል?

የክሊኒኩ ነርስ/አዋላጅ እንዲህ ያደርጋሉ፡

- ምን ዓይነት የአሰራር ሂደት እንደሚያስፈልግዎ ለማወቅ ግርዛትዎን ያያሉ
- ስላለብዎት የጤና ችግር ከእርስዎ ጋር ይነጋገራሉ
- የቀዶ ጥገናው እንዲካሄድልዎት ከወሰኑ፤ እንዴት እንደሚካሄድ እናስረዳዎታለን - የሚረዳ ከሆነ ስዕሎችን መጠቀም እንችላለን
- ከቀዶ ህክምናው በኋላ ሰውነትዎ እንዴት ሊለወጥ እንደሚችልና ስለ ማገገምዎ እንገልጽልዎታለን
- ሌሎች የጤና ችግሮች ካሉዎት ስለ ሌሎች አገልግሎቶች እና እንዴት ማነጋገር እንደሚቻል ልንነግርዎ እንችላለን
- እንዴት እንደሆኑ ለማየት ከቀዶ ህክምናው በኋላ ከ4 እስከ 6 ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ እንደገና እናይዎታለን።

የ FARREP ሠራተኛ እንዲህ ያደርጋሉ፡

- አንዳንድ ጊዜ የሴት ግርዛት ከሚከናወንባቸው ባህሎች ለመጣ ማንኛውም ሰው ድጋፍ ማድረግ
- ወደ ቀጠሮዎ እንዲደርሱ እና ከነርስ/አዋላጅ ጋር በቀጠሮዎ ወቅት አብረዎት በመገኘት ይረዳሉ
- ወደ ሆስፒታል እና ከሆስፒታል መጓጓዣ፤ መዋእለ ህጻናት፤ አስተርጓሚዎች እና ሌሎች አገልግሎቶች የመሳሰሉ ተግባራዊ ነገሮችን ያግዝዎታል
- በሆስፒታሉም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ ስለ ጠቃሚ አገልግሎቶች እና እንዴት እነሱን ማነጋገር እንደሚቻል መረጃ ይሰጡዎታል
- ስለ ግርዛት እና በቪክቶሪያ ያለው ህግ መረጃ ይሰጥዎታል

- ለእርስዎ እና ለሴት ልጅዎ/ጆችዎ (ካለዎት) የጤና መረጃ ይሰጥዎታል።

## ዝርዝር አድራሻዎች

የ FARREP ሠራተኞች ከሰኞ እስከ ዓርብ፣ ከጠዋቱ 9am ሰዓት እስከ ምሽቱ 5pm ሰዓት ድረስ ይገኛሉ

ተለፎን: (03) 8345 3058
ኢሜል: farrep.program@thewomens.org.au
ፋክስ: (03) 8345 3053

ወይም በአካባቢዎ ማህበረሰብ የጤና ማእከል ውስጥ የFARREP ሰራተኛን ያነጋግሩ።

ለበለጠ መረጃ በድረገጻችን ገብተው ይፈልጉ:
http://www.thewomens.org.au/health-information

## የቋንቋ አገናኝ መርበብ

**በርስዎ ቋንቋ መረጃ ለማግኘት በድረገጻችን ላይ ይጎብኙ**
للحصول على المعلومات بلغتكم زوروا موقعنا الإلكتروني
用您說的語言瞭解詳情，請瀏覽我們的網站
Για πληροφορίες στη γλώσσα σας επισκεφθείτε την ιστοσελίδα μας
अपनी भाषा में जानकारी प्राप्त करने के लिए हमारी वेबसाइट पर जाइए
Per informazioni nella vostra lingua visitate il nostro sito web
Macluumaad intaas ka badan oo af Somali ah booqo websaytkayaga
Kendi dilinizde bilgi almak için web sitemizi ziyaret edin
Để biết thông tin bằng ngôn ngữ của quý vị, hãy truy cập trang mạng của chúng tôi

## የቤተሰብ ጥቃት ድጋፍ

**የእርዳታ መስመር 1800 Respect National Helpline ይደውሉ**

ወሲባዊ ጥቃት፣ በቤት ውስጥ ወይም በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት ከደረሰብዎት እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።
በቀንም ሆነ በሌሊት በማንኛውም ሰዓት መደወል ይችላሉ።
1800 737 732
1800respect.org.au

**የክህደት ቃል:** ይህ የመረጃ ወረቀት አጠቃላይ መረጃን ብቻ ያቀርባል። ስለ ጤና አጠባበቅ የሚያስፈልግዎን ነገሮች በተመለከተ ግልጽ የሆነ ምክር ለማግኘት ከጤና ባለሞያዎ ምክር መጠየቅ ይኖርብዎታል። የሮያል የሴቶች ሆስፒታል (The Royal Women's Hospital) የጤና ባለሙያን ከማየት ይልቅ በዚህ የመረጃ ወረቀት ላይ በመተማመን ለሚደርስ ጉዳት ወይም ኪሳራ ምንም አይነት ሀላፊነት አይወስድም።።። አጣዳፊ የህክምና እርዳታ የሚያስፈልግዎት ከሆነ እባክዎ በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው የድንገተኛ አደጋ ክፍል ሂደው ያነጋግሩ።

© The Royal Women's Hospital 2025